**ሳምንታዊ ዜና (ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ብፁዕ አቡነ መርቆርዮስ አዲስ አበባ ይመጣሉ የተባለው ውሸት መሆኑ ተጋለጠ፣ አቡነ ሣሙኤልና አባ ገ/መድህን ከፍተኛ ፀብ ፈጥረዋል ተባለ፣ የፌዴራል ፖሊስ አባላት በዘረፋ ተግባር ላይ ተሰማርተው ሕዝቡን እያሰቃዩት ነው፣ ወያኔ የአንድ ብሄር ተወላጅ የሆኑ መኮንኖችን አስመረቀ፣ በአዲስ አበባ በሁለት ቦታዎች ወያኔ በለኮሰው እሳት በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት ወደመ፣ የድምጻዊ ቴዎድሮስ የፍርድ ቤት ውሎና ምስል ለምን አተማችሁ የተባሉ 4 የመፅሄቷ ሠራተኞች ለአንድ ሳምንት ታስረው ተፈቱ፣ ወያኔ ከጐንደር 40 ኪሎ ሜትር መሬት ቆርጦ ለሱዳን ሰጠ፣ በቦታው የሱዳን ታንከኛ ሰፈረ »**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌሎችም ዜናዎች በዝርዝር ያንብቡ.......**

የወያኔው መሪ ጋሻ ጃግሬ የሆኑት አባ ገ/መድህን በሀሰት የስደተኛው ሲኖዶስ መሪ አቡነ መርቆርዮስ ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ነው በሚል ያሰራጩት ዘገባ ሀሰት መሆኑ ተጋለጠ::

የወያኔ ቡድን ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በደረሰበት ከፍተኛ ኪሣራ ንፋስ እንደሚያዛውዘው ዛፍ ከወዲያ ወዲህ እየተላጋ ባለበት በዚህ ወቅት የክርስትና እምነት ተከታዩን ደጋፊ አድርጐ ለመያዝ በማሰብ በውሸት በፍፁም ሊሆን የማይችለውን በአቡነ መርቆርዮስ የሚመራው አሜሪካ ያለው ሲኖዶስ ወደ ሀገር ውስጥ መጥቶ ሊታረቅ ነው በሚል ያሰራጨት ዘገባ ሀሰት መሆኑን ብፁዕ አቡነ መልከ ፃድቅ አጋልጠዋል::

ውሸት ጉርሱ ዝርፊያ ትራሱ የሆነው የወያኔ ቡድን ቀንደኛ ደጋፊና አጨብጫቢ አባ ገ/መድህን የእነ መለስን ቡድን ለማስደሰት ሲሉ ብቻ ያልተሰራውን ተሰራ ያልተደረገውን ተደረገ በሚል ያለአንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ አቡነ መርቆርዮስ ሊመጡ ነው ተዘጋጁ በማለት በቤተክህነት ውስጥ አንድ ኮሚቴ አዋቅረው ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ እንዲነዛ ያደረጉ ቢሆንም ምርቱን ከግርዱ መለየት የሚችለው ሕዝብ በአባ ገ/መድህን ቡድን የሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ሳይታለል በጥሞና ሲከታተል የቆየ ሲሆን ሰሞኑን አቡነ መልከ ፃድቅ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መሆኑን በመግለፃቸው መላው የክርስትና እምነት ተከታዮች አባ ገ/መድህንን በትዝብት ውስጥ ከትቷቸዋል::

አቡነ መልከ ፃዲቅ በሰጡት መግለጫ በአቡነ መርቆርዮስ የሚመራው 18 ጳጳሶችን የያዘው ህጋዊ ሲኖዶስ ከአባ ገ/መድህን ጋር በፍፁም ያልተነጋገረ እና ስምምነት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ወደ ሀገር ውስጥ ብፁዕ አባታችን አቡነ መርቆርዮስ ይመጣሉ መባሉ ውሸት መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ገልፀው በእነ አባ ገ/መድህን የተጣሰው የቤተስክርስቲያኗ ቀኖና ተመልሶ ትክክለኛውን ቦታ እስካልያዘ ድረስ ይህ የማይሞከር ነው ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል::

በቤተክርስቲያን ህግና ደንብ የማይመሩት የወያኔው መሪ ነፍስ አባት አባ ገ/መድህን በቤተክርስቲያኗ እና በክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ የሚሠራው ግፍ እንዳለ ሆኖ በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን «ለምን ሕዝብን አስተማራችሁ» ብለው አንድ ባህታዊ በጥይት ያስገደሉ፣ በጐንደር አደባባይ እየሱስ አባ አምሀ እየሱስን

በፌዴራል ፖሊስ እያስደበደቡ ወደ ወህኒ ያወረዱ ግለሰብ ዛሬ የጌቶቻቸው ፖለቲካ ሲበላሽ የህዝቡን አንጀት ለማራራት ብፁእ አቡነ መርቆርዮስ ይመጣሉ ተብሎ ሀሰተኛ ወሬ መነዛቱ እጅግ በጣም የሚያሳፍር ነው ሲሉ ምዕመናኖች በቁጭት ይገልፃሉ::

በቤተክርስቲያኗ ህግና ደንብ ተከብሮ ያለ ይመስል፣ አንዳችም ጥፋት ያላጠፉ መስለው እንዲህ ያለ ሀሰተኛ ወሬ ማሰራጨታቸው እንዳሳዘናቸው የገለፁት አባ መልከ ፃዲቅ በአሁን ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ ሕግ እየተጣሰ፣ ዜጎቿ በኑሮ ውድነት ተቸግረው፣ የከፋ ድህነት እየተስፋፋ በአባ ገ/መድህን የሚመራው ቡድን ይህንን ደጋፊ ሆኖ መገኘቱ በጣም የሚያሳዝን መሆኑን ድርጊቱንም እንደሚያወግዙትና እንደሚቃሙት ገልፀዋል::

ዳር ድንበሯ የተጠበቀች ኢትዮጵያ መኖር አለባት መለያየትና መከፋፈል፣ በዘርና በጐሣ መለያየት ቀርቶ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወደ አንድነት ጐዳና እንዲገባ አሳስባለሁ ያሉት አባ መልከ ፃዲቅ ህዝቡ ከችግርና ከመከራ እንዲወጣም የዘወትር ፀሎታችን አይለየውም ሲሉም አክለው ገልፀዋል::

በአባ ገ/መድህን የሚመራው ቡድን የእምነት አባትነቱን ፈፅሞ በሳተ መልኩ በቤተክህነት ግቢ ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ መስፈሪያ ካምፕ ተሰርቶ ጥበቃውም የሚካሄደው በዚሁ አካል ሲሆን በተጨማሪ ካባ ለባሽ ደህንነቶችም የራሳቸው ቢሮ ተሰጥቷቸው አባ ገ/መድህንን ለመጠበቅና የሚባሉትን ወሬዎች ከቤተ ክህነት ሰራተኞችና ከውጭ እየለቃቀሙ ሪፖርት እንደሚያደርጉም ከቤተ ክህነት ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ::

እንደ ደርግ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም ፎቶዬ በሁሉም አደባባይ ይለጠፍ ብለው መመሪያ ያወረዱት አባ ገ/መድህን በሁሉም ቤተክርስቲያን ፎቶን ከመስቀል ይልቅ በጐ ተግባር ፈፅሞ በእምነቱ ተከታዮች ልብ መቀመጥ ይሻል ነበር ያሉት አንድ የጊዮርጊስ ደብር መምህር አሁን እያየነው ያለው የሶሻሊዝም ስርዓት ገና ጅማሮው ላይ የሚያራምድ መሪ መስለው ነው የሚታዩኝ ሲሉም አስተያየታቸውን ገልፀዋል::

በዚሁ ፎቶግራፍ መስቀል ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አቡነ ሣሙኤል ከእምነት አባት የማይጠበቅ ተግባር ነው በማለት አባ ገ/መድህንን ክፉኛ ሲነቅፏቸው እንደነበረ ያስታወሱት ምንጮች በአሁን ሰዓትም አቡነ ሳሙኤልና አባ ገ/መድህን ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገብተው እንዳሉ ምንጮቹ ገልፀዋል::

የተጋጩበት ዋነኛ ምክንያት ለጊዜው ከመግለፅ የተቆጠቡት ምንጮች የፀባቸው ጉዳይ ግን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ባለቤቱ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ድረስ እንደደረሰ በዝርዝር ይፋ አድርገዋል እኛም ይህንን ዝርዝር እንደደረሰን ይፋ የምናደርግ መሆኑን ከወዲሁ እንገልፃለን::

የወያኔው ቡድን ለስርዓቱ ጥበቃ ዋነኛ መሠረት ናቸው ብሎ ከትግራይና ከተቀረውም የሀገሪቷ ክፍሎች መልምሎ ያመጣቸው የፌዴራል ፖሊሶች በዘረፋ ተግባር ላይ ተሰማርተው ህዝቡን የቁም ስቃይ እያሳዩት መሆኑ ተጋለጠ::

የአለቆቻቸውን ባህርይ ያወቁት የፌዴራል ፖሊስ አባላት እነሱም ተመርቀው ወደ ስራ ከተሰማሩ ጥቂት ጊዜ ቢሆናቸውም ወደ ዘረፋ ተሰርማተው ሕዝቡን እያሰቃዩት ያለ ሲሆን ዘረፋው ጨለማን ተገን በማድረግ መሆኑንም የፌዴራል ፖሊስ ምንጮች አጋልጠዋል::

በቅርቡም በዚሁ ተግባር ላይ ተሰማርተው በገዛ ጓደኞቻቸው የተያዙ ሁለት የፌዴራል ፖሊስ አባላት የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ ተይዘው ወደ አለቆቻቸው ሲገቡ « ለምን ተመካክራችሁ እዚያው አትለቋቸውም» በሚል መልሰው በያዟቸው ፖሊሶች ላይ ያፈጠጡባቸው ሲሆን ፖሊሶቹ ለጊዜው አዲስ አበባ ኮሚሽን እስር ቤት እንደገቡ ለማወቅ ተችሏል ሲሉ ምንጮች አጋልጠዋል::

ከዚህ ቀደም በርካታ የፌዴራል ፖሊሶች በዚሁ ዘረፋ ተግባር ላይ ተገኝተው የተያዙት በርካቶች በነፃ የተለቀቁ መሆኑን የገለፀው ዘገባ ከላይ እስከታች በሙስናና በዘረፋ ተግባር የተሰማሩ በመሆኑ በዚህም የተነሳ ሀገሪቷንና ህዝቧን በድህነት አረንቋ ውስጥ እየከተቷቸው መሆኑ እየታየ ያለ ሀቅ ነው ሲሉም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ይገልፃሉ::

የወያኔ የማጥቂያ መሣሪያ ሆኖ በ24 ሰዓት የተመሰረተው ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተባለው መስሪያ ቤት የባለሥልጣን ሀብት ለመመዝገብ ረቂቅ አውጥቶ የነበረ ቢሆንም በእነ መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ጊዜውን ያልጠበቀ ወቅቱን ያላገናዘበ በመሆኑ ለጊዜው ይቅር በሚል ሀሳብ እንደገና ውድቅ ሊሆን እንደቻለ ለማወቅ ተችሏል::

የወያኔው ስርዓት ለእድሜዬ መጠገኛ ይሆኑኛል ያላቸውን ካድሬዎች በተለያየ የስራ መስክ ላይ አሰማርቶ እያሰራ ሲሆን፣ ሰሞኑንም በድግሪና በሰርተፍኬት የወታደራዊ መኮንኖቹን ማስመረቁን ይፋ አድርጓል::

ሚያዝያ 25 ቀን 2000 ዓ.ም ደብዘረይት በሚገኘው የወታደራዊ ተቋም ውስጥ ያስመረቃቸው መኮንኖች በአብዛኛው የሕወሓት ሲሆኑ ጥቂቶቹ ብቻ ለብሔር ስብጥር ይረዳሉ የተባሉ የወያኔ አቀንቃኞች እንዳሉበትም ከመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል::

በድግሪ ፕሮግራም ተመረቁ የተባሉት ከሻለቃ እስከ ኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው በመሉ የሕወሓት ካድሬዎች ሲሆኑ በሰርተፍኬት ተመረቁ የተባሉት መስመራዊ መኮንኖች በሙሉም ከጥቂቶች በስተቀር የሕወሓት መሆናቸውን የገለፁት ምንጮች ከዚህ ቀደም ወያኔ ከሚያደርገው በላይ የአንድ ብሔር የበላይነትን ለማንገስ ሆን ብሎ እየሰራ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ እነ መለስ ዜናዊ በሌሎች ብሔር ተወላጆች መኮንኖች ላይ እምነት ማጣታቸውን የሚያሳይ ነው ሲሉ ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል::

በዕለቱ መኮንኖቹን ያስመረቀው መለስ ዜናዊ ሲሆን የተገኙት ከፍተኛ ባለሥልጣናት በተለይም ጄኔራል መኮንኖቹ ሕወሓቶች መሆናቸውን የገለፁት ምንጮቹ መለስ ሰልፈኛውን ሲጐበኝ ከቀኝ ሳሞራ የኑስ ከግራ ሜ/ጄ/ል ዮሐንስ ገ/መስቀል መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በአዲስ አበባ ከተማ ሚያዝያ 26 ቀን 2000 ዓ.ም ከፍተኛ ድምፅ ያሉው ፍንዳታ መሰማቱ ተዘገበ፡፡ እሁድ ከምሽቱ 5:30 ላይ ፍንዳታው በመሿለኪያ አካባቢ የተሰማ ሲሆን፣ ስለደረሰው አደጋ እና ፍንዳታውን ያደረሰው ማን እንደሆነ ለጊዜው ያልታወቀ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል፡፡

16ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ውድድር ተጠናቀቀ በተባለበት ምሽት የደረሰው ይኸው ፍንዳታን ተከትሎ በአራት ኪሎ ለዘመናት የኖሩ አራት ሱቆች የእሳት ቃጠሎ እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከምሽቱ 5:30 ላይ አራት ኪሎ ከብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት ከሞቢል ጐን ከ1950ዎቹ ጀምሮ ተሰርተው ስራ ላይ የዋሉትን እነዚህ ሱቆች ወያኔ ካለው የንዘብ ፍቅር የተነሳ በእሳት አጋይቶ ካፈረሰ በኋላ ቦታውን በጨረታ ለመሸጠ በማሰብ የፈፀመው መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡

ለብዙ ዓመታት በልብስ ስፌትና በሱቅነት፣በእስቴሽነሪነትና በቡቲክነት ሲገለገሉበት የነበሩትን እነዚህ አራት ሱቆች ወያኔ ቦታውን ለመሸጥ ሲል ብቻ በውስጡ በብዙ መቶ ሺህዎች የሚገመት ንብረት እንደያዙ ሰው በሌለበት ጭር ማለቱን አይቶ በእለቱ እሳት የተለኮሰ ሲሆን፣ ሱቆቹ ወዲያውኑ የጋዩ መሆኑም ታውቋል፡፡

እሣቱ እንደተያያዘ የእሣት አደጋ መኪና መጥቶ ምንም መከላከል ያላደረገ ሲሆን አጠገቡ ያለው ነዳጅ ማደያ እንዳይነካ ብቻ እየተቆጣጠሩ ሲቆቹ እስኪነዱ መጠበቃቸውን በወቅቱ በድብቅ ሲከታተሉ የነበሩ የአይን እማኞች ገልፀው ይህ የወያኔ የሁልጊዜ ሥልት በመሆኑ ሊደንቀን አይገባም ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ ሰኞ ሚያዝያ 27 ቀን 2000 ዓ.ም የአርበኞች ቀን በሚከበርበት ዕለት የመንግስትና የድርጅት መስሪያ ቤት ዝግ ሆኖ የዋለ ሲሆን፣ ማንም በሌለበት በመርካቶ በተለምዶ ቦምብ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የአዋሽ ባንክ ላይ እሳት ተለኩሶ በሚለዮን የሚቆጠር ንብረት እንዲወድም መደረጉን ከአይን እማኞች ገለፃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከቀኑ 9:30 ላይ የተነሳው ይኸው እሳት ሆን ተብሎ በተቀነባበረ ዘዴ መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ወያኔዎች በተለይ አዋሽ ባንክን ከተቃዋሚ ድርጅት ደጋፊነት ጋር በማያያዛቸው ውስጡ ያለው ንብረት (ገንዘብ) እንዲውድም ሆን ብለው ያደረጉት መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ወያኔዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሕዝብ ንብረትና

ሀብትን ከማውደም ወደ ኋላ የማይሉ መሆናቸውን ያረጋገጡበት መሆኑን ያሳያል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

ሥራ በሌለበት እንቅስቃሴዎች በተገደቡበት ስፍራ አጥንተውና አቅደው በጠራራ ፀሀይ 9:30 ላይ የለኮሱት እሣት የእሣት አደጋ ሠራተኞች በቀላሉ ደርሰው ማጥፋት ሲችሉ ባልታወቀ ምክንያት ቃጠሎው ከተከናወነ በኋላ በመድረሳቸው በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት የወደመ መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ወያኔ በተለየ በግል ባንኮች ላይ ካለው የተቃዋሚ ኃይሎችን ይረዳሉ የሚል ጥላቻ ድርጊቱን የፈፀመው እሱና እሱ ብቻ መሆኑን ያረጋገጠ ነው ብለዋል፡፡

የአለም ሕብረተሰብን ለማታለል ሲል በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የፕሬስ ሕግ አርቅቀን ሚኒስትሮች ም/ቤት አፅድቆ ለተወካዮች ም/ቤት የቀረበ መሆኑን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ለታዋቂው መፅሄት ኒውስ ዊክ የገለፀ ቢሆንም ተግባሩ ግን እጅግ የሰማይና የምድር ያህል እንደሚለያይ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ የተሰማሩ ዜጐች ገለፁ፡፡

ሰሞኑን የቴዎድሮስ ካሣሁንን የፍርድ ቤት ውሎ ከምስል ጋር በማስደገፍ ለንባብ ለማብቃት ተዘጋጅታ የነበረችው ዕንቁ መፅሄት በደህንነት ኃይሎች የታገተች ከመሆኑም በላይ 4 ሰዎች ከመፅሄቷ ጋር በተያያዘ ታፍሰው ለእስር እንደተዳረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የወያኔ ንብረት የሆነው ብራና ማተሚያ ቤት ከሌሎቹ የሀገሪቱ ውስጥ ማተሚያ ቤቶች በዋጋ የተሻለና በወረቀት ጥራት ጥሩ ነው ብለው በማሰብ ወደ ህትመት የገቡት የዕንቁ መፅሄት አዘጋጅና አሳታሚዎች ከረቡዕ ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምረው ከማተሚያ ቤቱ ጋር ሲሰሩ ቆይተው 10ሺ ኮፒ ታትሞ ካለቀ በኋላ የፊት ለፊት ገፁ የቴዲ አፍሮና ከጀርባው የፍርድ ቤት ሂደቱን ሲከታተል የነበሩ የህዝብ ብዛት ያለበትን ምስል የተመለከተው የብራና ማተሚያ ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ የሕወሓቱ ሰው አብርሃ ሐጐስ ደህንነቶችን በስውር ጠርቶ አርብ ከምሽቱ 3ሰዓት ላይ መፅሄቷን በሚኒባስ መኪና ጭነው ሲጓዙ በቁጥጥር ስር መዋላቸውንና መፅሄቱንም መውረሳቸው ታውቋል፡፡

የውሸት ነጋሪት እየጐሰመ የሚለፍፈው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የተዋጣለት የፕሬስ ሕግ አለን እያለ ገንዘብ መለመኛ እያደረገው ሲሆን፣ በተጓዳኝ የቴዲ ምስልን እና የፍርድ ቤት ውሎን አትታ ባወጣችው ዕንቁ መፅሄት ላይ ይህንን የመሰለ አስነዋሪ ተግባር መፈፀሙ በቴዲ ላይ የሰሩት ሸፍጥ ሊያጋልጣቸው መሆኑን በመረዳታቸው ብቻ ለማገት እንደተገደዱ ያጋለጡት የህግ ባለሙያዎች ተወደደም ተጠላ የወያኔ የፍርድ ቤት አሰራር ከዜሮ በታች መሆኑን አለም አቀፍ የሕግ ባለሙያ ማህበራት በሙሉ የተረዱ መሆኑን ያወቁት ወያኔዎች ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል እየተጓዙ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የመፅሄቷ ምክትል አዘጋጅ አለማየሁ ማህተመወርቅን ጨምሮ ኢሳያስ የተባለው የመኪናው ሹፌር፣ ታህሳስ ወርቁ ህትመት ክትትል፣ ሰለሞን መኮንን ረዳት የዕንቁ መፅሄትን ከማተሚያ ቤት ጭነው ሲጓዙ ማተሚያ ቤቱ በራፍ ላይ በማገት 4ቱንም ወደ አዲስአበባ ፖሊስ ኮሚሽን እስር ቤት ወስደው እንዳሰሯቸው ለማወቅ ተችሏል።

ከ4 ቀን በኋላ ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የልደታ ምድብ ችሎት ፊሊፕስ ህንፃ አጠገብ በሚገኘው ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን፣ ወደ ፍርድ ቤት ሲገቡ በሰንሰለት እጆቻቸውን ታስረው እንደነፍሰ ገዳይ ያቀረቧቸው መሆኑም ታውቋል።

ፍፁም ከፕሬሱ ጋር ምንም ተያያዥነት በሌለው ፍርድ ቤት ውስጥ የቀረቡት የዕንቁ ምክትል ዋና አዘጋጅና ባልደረቦቻቸው የተጨማሪ 14 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው ለግንቦት 11 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲቀርቡ በሚል የተወሰዱ ቢሆንም ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፖሊስ ፅህፈት ቤት ዋስትና አስይዘው መለቀቃቸው ታውቋል። በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ጽ/ቤት እስር ቤት ውስጥ በጭለማ ቤት ታስረው የነበሩት እነዚሁ የእንቁ መፅሄት ባልደረቦች ማንም ሰው እንዳያያቸው ታግደው እንደነበርም ለቤተሰቦቻቸው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

የቴዲ አፍሮን የፍርድ ሂደት ተከታትሎ በመስል አስደግፎ ለማውጣት የታተመችው መፅሄት የታገተችው በወያኔ ባለሥልጣናት ትዕዛዝ በደህንነት ሠራተኞች ፈፃሚነት ይሁን እንጂ መርማሪ ፖሊሶች ጉዳዩን ከተመለከቱ በኋላ የሚከሰሱበት ምክንያት ግራ እንዳጋባቸው በመግለፅ እርስ በእርስ ሲነጋገሩ እንደነበረም ምንጮች ጠቁመዋል። ቴዲ አፍሮ ለወያኔ የራስ ምታት ሆኖ እንዲህ ወጥሮት መኖሩን ያወቅነው አሁን ነው ያሉት አንድ መምህርት የቴዲን ምስል ለምን ታትማላችሁ ብሎ ሀገርና ሕዝብ ያወቀውን ፀጋይ የሞቀውን እውነት ለምን ፃፋችሁ ብለው ለዚያውም ጉዳዩ በማይመለከተው ፍርድ ቤት ማቅረባቸው በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑን ያሳያል ሲሉም ገልፀዋል።

ቴዲ አፍሮ ለግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ይሰጣሉ ተብሎ ፖሊሶችን ለማቅረብ የተቀጠረ ቢሆንም በአለም አቀፍ ደረጃ ቴዲ ይፈታ የሚለው ዘመቻ ተቀጣጥሎ እንደቀጠለ መሆኑን ከተለያዩ አገሮች የደረሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ።

ባለፈው ሳምንት በአሜሪካ በወያኔው ኤምባሲ በር ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ተገኝቶ ተቃውሞውን ያሰማ ሲሆን፣ አንድም የኤምባሲው ሠራተኛ በፍርሀት ብቅ ሳይል መቅረቱን የገለፀው ዘገባ ሰሞኑንም በእግሊዝ ለንደን ከተማ «ቴዲ ይፈታ ያለኃጢያቱ ነው የታሰረው » በሚል ከፍተኛ ተቃውሞ ሰልፍ መደረጉን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ወያኔ የቴዲ አፍሮን ሥራዎች በመፍራት ብቻ ያለሥራውና ኃጢያቱ በሀሰተኛና በፈጠራ ክስ ወንጅሎ ለእስር ቢዳርገውም ተቃውሞ ከውጭና ከውስጥ ያየለበት ወያኔ ምናልባትም ደጋፊዎቹ አጥር ሰብረው ያስፈቱታል በሚል ፍራቻ ለብቻው በተከለለ አጥር ጠባብ ክፍል ውስጥ አስረውት እንደሚገኙም ታውቋል፡፡

ሀገርና ህዝብን የሚከፋፍለው ወያኔ ሰሞኑን ከጐንደር መሬት ቆርሶ ለሱዳን መስጠቱን እና በቦታውም የሱዳን ሠራዊት እንዲሰፍር ማድረጉን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

የወያኔው ቡድን ከሱዳን መንግስት ጋር በምስጢር ተስማምቶ የኢትዮጵያን መሬት 40 ኪሎ ሜትር ያህል ቆርሶ የሰጠ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በቦታው ላይ በታንክ የታገዘ የሱዳን ሠራዊት እንዲሰፍር መደረጉንም ጨምሮ ገልጿል፡፡

ነዳጅ ድጐማ እንዲደረግለት በመስማማት 40 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው መሬት ከጐንደር ላይ ቆርሶ ለሱዳን የሰጠው ወያኔ ለዘመናት ታፍራና ተከብራ የኖረችውን ሀገር እንደዳቦ ዙሪያዋን እየፎረፎተ ታሪክና ባህሏን እያበላሸው ያለው መርዘኛው ወያኔ ሰሞኑን የሰጠው መሬት ከሱዳን ድንበር እስከ ወለጋ ጫፍ የባቡር መስመር 1600 ኪሎ ሜትር ርዝመት እንዲዘረጋ ስምምነት ተፈራርመናል ብሎ ባወጀበት ሰዓት መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ይህንኑ መሬት ለሱዳን ሰጥቶ ቦታው ላይ የሱዳን ሠራዊት ሠፍሮ የነበረ ቢሆንም የጐንደር ህዝብ እምቢ ለሀገሬ በማለት ውጊያ ገጥመው መኮንኖችን ጨምሮ 20 የሱዳን ወታደሮችን ገድለው ቦታውን ያስለቀቁ ቢሆንም የወያኔው ቡድን መልሶ አሁን 40 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ከኢትዮጵያ ላይ ቆርሶ የሸጠ መሆኑን ለማንም ዜጋ የሚያንገበግብና የሚያቃጥል መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል፡፡

ከወራት በፊት ጀምሮ በተደጋጋሚ ጊዜ በዚህ ዙሪያ ወያኔ በምስጢር ከሱዳን ጋር ተመሳጥሮ መሬት ቆርሶ ሊሸጥ መሆኑን የዘገብን ሲሆን ያልነው ሳይቀር ዛሬ መሸጡን በይፋ ማወጁ ታውቋል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ይህንን አስመልክቶ የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት የሆነው ግለሰብ ተጠይቆ ውሸት እንደሆነ ሲለፍፍ የነበረ ቢሆንም ዛሬ በሀገርና በህዝብ ላይ የሰሩት ሸፍጥ ተጋልጦ የወያኔን ገመና እርቃኑን መቅረቱ ታውቋል ሲል የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡